# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከዲሴምበር 21-31 የነበረው የአየር ሁኔታ  ግምገማ እንዲሁም

## ከጃንዋሪ 1-10 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጃንዋሪ 2022
አዲስ አበባ

| ርዕስ | ገፅ |
|---|---|


እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ........ 1
ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ........ 2
ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2021 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት........ 3
ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ........ 4
ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር........ 4
እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ ........ 5
በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 5
ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ........ 5
እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 6
ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 6
እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ ........ 7
እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ........ 7
እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 8


# እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የበጋዉ ደረቅ፣ ፀሃማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡብና በምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ ከሞላ ጎደል ቀጥሎ ተስተዉሏል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም የለሊትና የማለዳዉ ቅዝቃዜም በተጠቀሱት አካባቢዎች ላይ የቀጠለ ሲሆን፤ የቀኑ ዝቅተኛ ሙቀትም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስም በሀረማያ 1.8፣ በደብረብርሃን 2.0፣ በአርሲ ሮቤ 3.5፣ በቢሾፍቱ 3.3፣ በአደሌ 4.0 እና በመሃል ሜዳ 4.2 በዲግሪ ሴልሽየስ ይገኙበታል፡፡ በሌለ በኩል አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ከነበረዉ የደመና ሽፋን በምዕራብና መካከለኛዉ አማራ፣ በምዕራብ ኦሮሚየ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡


ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በኢሉባቦር፣ በጅማ፣ በምስራቅና ቄለም ወለጋ እንዲሁም በቦረና ዞኖች፣ በአኙዋክ፣ በከፋ፣ በሸካ፣ በቤንች ማጂ፣ በደቡብ ኦሞ፣ በጋሞና ጎፋ፣ በጥቂት የሰሜንና ደቡብ ጎንደር ዞኖች ላይ ከ5-70 ሚሜ የሚደርስ ከ2-6 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በጥቂት የሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ በምዕራብ ጎጃም፣ በጋምቤላ ክልል ሁሉም ዞኖች፣ በሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ በኢሉባቦር፣ በጅማ፣ በሸካ፣ በከፋ፣ በቤንችማጂ፣ በደቡብ ኦሞ፣ በጋሞና ጎፋ፣ በኮንታ ልዩ ወረዳ እና ዳዉሮ ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ካርታ 3) ፡፡


ካርታ 1 ኢ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2   እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2021 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 3 ኢ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር





ከመደበኛ በታች    መደበኛ    ከመደበኛ በላይ

# እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት የዲሴምበር ሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስተዋለ እንደነበር የተተነተኑ የሚትዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ይህም ሁኔታ የመኸር አብቃይ በሆኑት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው ደረቅ የአየር ሁኔታ በመካሄድ ላይ ላለው ድህረ ሰብል ስብሰባ አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር። ከደረቃማውና ከነፋሻማው የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሌሊት እና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በአንዳንድ በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡብና ምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ ከሞላገደል ቀጥሎ ተስተዉሏል፡፡ ከቅዝቃዜው መጨመር ጋር  በአንዳነድ አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ይህም ሁኔታ በመስኖ በመታገዝ በሚለሙ በፍራፍሬ ተክሎችና በጓሮ አትክልቶች ላይ በጥቂት ቦታዎች ላይ በተወሰነ መጠን አሉታዊ ጎን ነበረው፡፡ በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ከነበረዉ የደመና ሽፋን በምዕራብና መካከለኛዉ አማራ፣ በምዕራብ ኦሮሚየ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት የተመዘገበ ሲሆን ይህም የተገኘዉ እርጥበት  ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት በተወሰነ መልኩ በጎ ገጽታ ነበረው (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ከዲሰምበር 21-31/2021 የነበረው የእርጥበት ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ የላይኛውና የመካከለኛው ባሮአኮቦ፣ በጥቂት የታችኛውና የመካከለኛው ኦሞጊቤ እና የታችኛው ገናሌዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ አግኝተዋል፡፡ በተቀሩት በአብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ ግን ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ ተስተውሏል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ እርጥበት የተስተዋለባቸው ተፋሰሶች ላይ የተገኘው ውሃ ለውሃ ሀብት ግብዓት በጎ ጎን ነበራቸው (ካርታ 5) ፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በአሁኑ ጊዜ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየታየ ያለው የበጋው ደረቃማ የአየር ሁኔታ ቀጣይነት እንደሚኖረው የሚጠበቅ ቢሆንም፣ በአንዳንድ ደጋማ አካባቢዎች ላይ የሌሊቱ እና የማለዳው ቅዝቃዜ በአንፃሩ ሊቀንስ እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በሌላ በኩል በመጨረሻዎቹ ጥቂት ቀናት ወደ ሀገራችን መጠነኛ እርጥበት አዘል አየር እንደሚገባ በመጠበቁ በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የደመና ሽፋን ሊኖር እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ቦታዎቻቸዉ ላይ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ሊያገኙ እንደሚችሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

## ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ በጃንዋሪ የመጀመሪያው አሥር ቀናት ደረቃማው የአየር ሁኔታ ከማዘንበሉ ጋር ተያይዞ በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሰብል ስብሰባው ተጠናቅቆ የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራት በስፋት የሚስተዋልበት ወቅት ነው፡፡ በሌላ በኩል ከደረቃማው የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የበጋው ወቅት የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ በቀጣይነት የሚስተዋልበት ጊዜ ነው፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በሚቀጥለው የጃንዋሪ የመጀመሪያው አስር ቀናት በሁሉም የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ እንደሚቆይና በአንዳንድ ቦታዎች ላይም የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ቀጣይነት እንደሚኖረው በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ ላይ ተመልክቷል፡፡ በተለይም የሚጠበቀው ደረቃማው የአየር ሁኔታ በመከናወን ላይ ለሚገኘው የድህረ ሰብል ስብሰባ እንቅስቃሴ በጎ ጎን ይኖረዋል፡፡ በአንጻሩም ከደረቃማውና ከነፋሻማው አየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ደጋማ አካባቢዎች ላይ ቅዝቃዜው በቀጣይነት እንደሚስታዋል የትንበያ መረጃዎች አመልክተዋል፡፡ ይህም ሁኔታ በተለይም እድገታቸውን ሙሉ በሙሉ ባልጨረሱ ሰብሎች፣ እንዲሁም በመስኖ በመታገዝ በሚለሙ በፍራፍሬ ተክሎችና በጓሮ አትክልቶች ላይ አሉታዊ ጎን ሊኖረው እንደሚችል ነው፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሮች እነደ አካባቢው ሁኔታ የሚኖረውን ቅዝቃዜ ለማሻሻል የሚረዱ የተለመዱ ተግባራትን ለማከናወን የበኩላቸውን ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ ከወዲሁ ይመከራሉ፡፡ በሌላም በኩል በመጨረዎቹ ጥቂት ቀናት አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩ ዝናብ ሰጭ

የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በተለይም በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው እርጥበት ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት ከማሻሻል አንፃር ጠቀሜታ ያለው ከመሆኑም በተጨማሪ የበልግ ወቅትን ቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች ማሳን አስቀድሞ ለማዘጋጀት ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ እየታየ ያለው የበጋው ደረቃማ የአየር ሁኔታ ቀጣይነት እንደሚኖረው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በሌላ በኩል በመጨረሻዎቹ ጥቂት ቀናት ወደ ሀገራችን መጠነኛ እርጥበት አዘል አየር እንደሚገባ በመጠበቁ በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የደመና ሽፋን ሊኖር እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በጥቂት የላይኛው ባሮአኮቦ፣ መካከለኛው አባይ፣ የላይኛውና የመካከለኛው አዋሽና አፋርደናክል፣ የመካከለኛውና የታችኛው ኦሞጊቤ እንዲሁም የላይኛውና የመካከለኛው ስምጥ ሸለቆ አዋሳኝ ቦታዎች ጨምሮ በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው የእርጥበት መጠን እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡